وجاء شهر رمضان

የረመዷን ወር መጣ

إعداد: الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም፡ አቡ'ዓብዱልዓዚዝ/ዩሱፍ አሕመድ

بسم الله الرحمن الرحيم

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባው ነው። እናመሰግነዋለን ፤ በእርሱም እንታገዛለን ፤ ይቅርታም እንጠይቀዋለን ፤ ከሓጢያታችን ወደርሱም ተጸጽተን እንመለሳለን። ከነፍሶቻችን ተንኮል ፣ ከተግባሮቻችን ክፋት በአላህ እንጠበቃለን። አላህ የመራውን ማንም አያጠመውም፤ አላህ ያጠመመውን ደግሞ ማንም አይመራውም። ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የሌለ መሆኑን ፤ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ ደግሞ አገልጋዩና መልክተኛው መሆናቸውን በእርግጠኝነት እመሰክራለሁ።

የአላህ ውዳሴና ሰላምታ በነብዩ ሙሐመድ ﷺ ፣ በቤተሰቦቻቸው ፣ በአጠቃላይ በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን።

ከዚህ በመቀጠል፡

ሙእሚኖች የዲናቸውን ጉዳይ ተቀራርበው የሚተዋወሱበት መልካምና የተከበረ ወር ፊት ለፊታቸው ተደቅኖ ይጠብቃቸዋል። በዚህ በተከበረ ወር ውስጥ ተቆጥረው የማያልቁ ታላላቅ ፋይዳዎችና መልካም ነገሮች ስለሚገኙ ሙስሊሞች በመልካም ዝግጅት በንቃት ሊጠባበቁት ይገባል።

ሙስሊም የሚከተለውን ትክክለኛ ሐዲስ ዘግበዋል፡-

አንድ ቀን ነብዩ ﷺ መስጅድ ድንገት ሲገቡ ሶሃቦቹ ተቀምጠው በዲን ጉዳይ እየተዋወሱ አገኟቸው።

“ምን አስቀመጣችሁ? አሏቸው። “ስለኢስላምና አላህ በእኛ ላይ ስለዋለው መልካም ውለታ እየተዋወስን ነው” አሏቸው። የአላህ መልእክተኛም “አስኪ በአካህ ማኩ !

ይህ አንጅ ሌላ ያስቀመጣችሁ ጉዳይ የለም?" በማለት ጠየቋቸው። "ወሏሂ! ይህ እንጅ ሌላ ያስቀመጠን ጉዳይ የለም።" በማለት ሶሃቦች ምላሽ ሰጡ። የአላህ መልእክተኛም "ወኳሂ! እኔ እናንተን ተጠራጥሬ አይደለም በአኳህ ስም ያስማልኳችሁ። ነገር ግን ጅብሪል አሁን መጦ አላህ በእናንተ ጉዳይ በመላኢካዎች ላይ እንደሚፎካከር ነገሮኝ ነው (የሄደው)።" አሏቸው። *(ሙስሊም፡2702)*

ይህ ሐዲስ ፣ ከሁሉም በላይ ከፍ እንዲደረግና በውስጡ የእርሱ ስም ብቻ እንዲወሳ ባዘዘበት ቤት ውስጥ እርሱን በማውሳት ተጠቃሚ ላደረገውና ላከበረው ሰው ታላቅ የሆነ ጥቆማ አለው።

በዚህ ዓይነቱ የተባረከ ቦታ እያንዳንዱ ሙስሊም ተጠቃሚ ሊሆን ዘንድ ካለው ጊዜ ቀንሶ ነፍሱን እርሱን ብቻ በመገዛት ሊያስታግሳት ይገባል። ነገር ግን ማብቂያ በሌለው የዱንያ ሐጃና ለሁለቱም አገር በማይጠቅም የዛዛታ ወሬ ከተጠመደ ፤ ከአላህ ፊቱን ካዞረ የመልካምና የአላህን ውዴታ ማግኛ መስመሮችን በቀላሉ ማወቅም አይችልም ፤ ለእርሱም የተገሩ አይሆኑም።

መስጅድ ፣ የዲን ጉዳይ ምክር ይሰጥበታል ፣ አላህ ይወሳበታል ፣ ልቦች ማነቃቂያ ያገኙበታል ፣ ወደመልካም ስራዎች ቅስቀሳ ይደረግበታል ፣ በአጠቃላይ ሰዎች ታላላቅ ጥቅሞችን ያገኙበታል።

ይህችን እጥር ምጥን ያለች መጽሐፍ ለአንባቢያን ለማቅረብ ያነሳሳኝ ዋና ዓላማ የረመዷን ወር በመቅረቡ እንዴት አድርገን ይህን የተከበረ የረመዷን ወር እንቀበለው በሚለው ጉዳይ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮችን ለማስታወስ ነው። እንደምታውቁት የረመዷን ወር ሊገባ ጥቂት የሚባሉ ቀናቶች ብቻ ነው የቀሩት።

ይህ የተከበረ ወር ሰፊ በሆነው መልካሙ ፣ በተከበሩ ትሩፋቶቹ ፣ ተከታታይ በሆኑ በረከቶቹ ፊቱን አዙሮ ወደኛ ቀርቧል። መምጣቱን ፣ መግባቱን ሲቋምጡ ፣ ሲጠባበቁ ለነበሩ ፣ ከነፍሳቸው ውሥጥ ታላቅ አሻራ እንደሚጥል ለተገነዘቡ ሙስሊሞች ትልቅ ቦታ ይኖረዋል። ወሩ ከሌሎች ወሮች የሚለይና በወሩ ውስጥ ያለውን ታላቅ በረከትና መልካም ነገሮች የሚያውቁ በመሆናቸው እርሱ የገባ ጊዜ በሐሴት ይዋጣሉ ፤ እርሱ በመቅረቡ አንዱ ሌላውን ያበስራል።

አላህ እድሜን ለገሶት እርሱን በመታዘዝ ወደአላህ የምንቃረብበት ፣ በውስጡ የሚገኙ በረከቶችን ከሙስሊሞች ጋር የምንቋደስበት ለሆነው ታላቅ የኢማን ወር በክብር ያደረሰው ሰው ታላቅ ችሮታን ተጎናጽፏል።

የዚህን የተከበረ ወር መምጣት ነብዩ ﷺ ለሶሃቦቻቸው ማብሰራቸው በትክክለኛ ሐዲስ ተዘግቦ ይገኛል።

ረሡል ﷺ ለሶሃቦች የሚከተለውን ይሉ ነበር፡-

“የጀነት በሮች የሚከፋፈቱበት ፣ የጀሀነም በሮች የሚዘጋጉበት ፣ ሰይጣናት የሚተሳሰሩበት ፣ በውስጡ ከአንድ ሸ ወር የምትበልጥ አንዷት ሌሊት ያለበት የተባረከ የረመዷን ወር መጣላችሁ። አርሱን መጾም አላህ በእናንተ ላይ ግዴታ አድርጓል። (ከመልካም ነገር) በአርግጥ የተከለከለው ፤ ከአርሷ መልካም የተከለከለ ሰው ነው።”

(አህመድ፡ 8991, ነሳኢ፡ 2106)

“የረመዷን ወር መጣላችሁ” በዚህ የተረጋገጠ ንግግራቸው ውስጥ ብስራት አለበት። ይህ ወር ቀልባችሁን ወደአላህ የምታዞሩበት ፣ ከነፍሳችሁ ጋር ሂሳብ የምታደርጉበት ፣ አላህ ባዘዘው የምትቆሙበት ፣ ከሀራም ነገሮች የምትርቁበት ፤ በአጠቃላይ ጤና ፣

ሰላም ፣ ኢማን የምታገኙበትና በኢስላም ጸጋን የምትጎናጸፉበት ወር መጣላችሁ ማለታቸው ነው።

ይህ ንግግር የዚህን ወር ታላቅ ግምትና ደረጃ ለመገንዘብ ልብን የሚያንቀሳቅስ ጠቋሚ ምልክት ያለበት ሲሆን እርሱም ይህ ወር መጧልና ተዘጋጁ ፣ መልካም አቀባበልም አድርጉለት ፣ አስተናግዱት ማለት ነው።

የሰው ልጅ ታላቅና አንገብጋቢ የሆነ ነገር ፊት ለፊቱ ሲመጣ አቀባበል ለማድረግ ሽር ጉድ ይላል፣ አንዱ ሌላውን ያበስራል ፣ ከባድ የሆነ መስተንግዶ ያዘጋጃል።

የረመዷን ወር ፣ በሙእሚኖች ነፍስ ውስጥ የተከበረና ውድ የሆነ እንግዳ ነው። ማንኛውም ሙእሚን ይህ የተከበረ እንግዳ በመምጣቱ ነፍሱ በሐሴት ትሞላለች። አንድ ሰው ክቡር ፣ ደረጃው ከፍ ያለና ውድ የሆነ እንግዳ ይመጣል በተባለ ጊዜ በምን አይነት ሁኔታ እንደሚያስተናግደው ሲያስብ ሲጨነቅ አላስተዋልክምን?

“የረመዷን ወር መጣላችሁ” ይህን ውድ የሆነ እንግዳ በክብር ተቀብለን በክብር ለመሸኘት ሐቁን በአግባቡ ለመወጣትና ለማሟላት ነፍሳችሁን አዘጋጁ። ጌታችሁን ስትገናኙ ለሚያስደስታችሁ ታላላቅ የዒባዳ አይነቶች ተዘጋጁ። ምክንያቱም ይህ ክቡር እንግዳ ፈጥኖ እንደመጣው ሁሉ ፈጥኖ ይሄዳል።

ሙስሊሞች የረመዷንን ወር በመልካም ሊቀበሉ ይገባል። ይሁን እንጅ አቀባበላችን እንደሰዎች ሊለያይ ይችላል።

1. አንዳንዶች ልክ ይህ ወር የምግብ ወር እስኪመስል ድረስ ወደገበያ ተሽቀዳድመው በመውጣት የተለያዩ የምግብ አይነቶችን በመግዛት አቀባበል

የሚያደርጉ አሉ፡፡ ተመልከታችሁ ከሆነ አንዳንድ ሱቆች በረመዷን ወር ከሌሎች ወሮች በተለየ ሁኔታ አቅርቦታቸውም ዋጋቸውም የሚጨምር አለ፡፡ በዚያው ልክ አንዳንድ ቤተሰቦች ማፍጠሪያ ሰዓት ከምግብ ማእዳቸው ላይ የሚቀርበው የተለያየ ምግብ ከአቅም በላይ በመሆኑ ቤተሰቡ ሳይጠቀምበት በቀላሉ የሚበላሽ አለ፡፡

2. ሌሎች ደግሞ የረመዷን ወር ሊገባ ሲል ቀድመው የጊዜ ማሳለፊያ መጫዎቻ ጌሞችን እና የመሳሰሉ መዝናኛ እቃወችን ገዝተው (ፊልሞችን አዘጋጅተው) የሚያስቀምጡ አሉ፡፡ ይህን በርካታ ጥቅሞች ያሉበትን የተከበረ የረመዷን ወር በማይረቡና በማይጠቅሙ ነገሮች ያሳልፋሉ፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ ጊዜ የተረጋገጠ ጉዳት ሆኖ እናስተውላለን፡፡
3. ሌሎች አላህ የመረጣቸው ፣ በእዝነቱ በእንክብካቤው ያገዛቸው ሰዎች ደግሞ ነፍሳቸውን ከወዲሁ ለዚህ የተከበረ ወር የሚያዘጋጁ ናቸው፡፡ በርካታ መልካም ነገሮችን ከወዲሁ ለመስራት በአዕምሯቸው ያንሰላስላሉ፡፡ ለቁርኣን ፣ ለዚክር ፣ ለሌሊት ሶላት ፣ ሰዎችን ለመርዳት ፣ ለምስኪኖች ለመሶደቅ እና ለዒልም ፕሮግራሞችን ያወጣሉ፡፡ የረመዷንን ወር በእነዚህ መልካም ተግባራት ተጠምደው ያሳልፋሉ፡፡
4. አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በአላህ ትዕዛዛት ላይ ለመቆም የተለያዩ የመልካም ስራ ፕሮጀክቶችን ቀርጸው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ሰፊ የሆኑ የመልካም ስራዎችን በመስራት ወቅት ጠቧቸው የጀመሩትን ስራ ሳያጠናቅቁ ወሩ የሚያልቅባቸው ሰዎች ናቸው፡፡
5. አንዳንዶቹ ደግሞ የረመዷን ወር ልክ እንደሌላው ወር እኩል የሚሆንባቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ሌሎች ወሮች እንደሚያልፉት የረመዷን ወር እንዲሁ በቀላሉ ያልፋል፡፡ ደረጃው ከአንድ ሽ ወር ዒባዳ ይበልጣል የተባለለት ሌሊት እንኳ ልክ ከሌሎች ሌሊቶች ጋር በተመሳሳይ የሚያሳልፉ ሰዎች አሉ፡፡

6. ይህ ከሙስሊም ጋር የማይሄድ ፣ ግልጽ የሆነ ኪሳራ ነው።

✓ ስለዚህ እኛ ሙስሊሞች ይህን የተከበረ ወር በደንብ ልንቀበል ፣ ደረጃውን አውቀን እንግድነቱን ልናሳምር ፤ ነፍስን ለዒባዳ ፣ በውስጡ ለሚገኙ በርካታ ጠቃሚ ነገሮች ልንሽቀዳደምና ልንዘጋጅ ፤ በአጠቃላይ የዚህ ወር እውነተኛ ቤተሰብ ልንሆን ይገባል።

ቲርሚዝይ እና ኢብን ማጀህ በዘገቡት አቡሁረይራ رضي الله عنه የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

የአላህ መልክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

“ከረመዷን ወር የመጀመሪያው ሌሊት ላይ የጅን አመጸኞችና ሰይጣናት ይተሳሰራሉ። የእሳት በሮች ይዘጋጋሉ። ከእርሷ አንድም በር አይከፈትም። የጀነት በሮች ይከፋፈታሉ። ከእርሷ አንድም በር አይዘጋም። “አንተ መልካም ፈላጊ ሆይ! ፊትህን ወደ (አላህ ትዕዛዝ) አዙር ፤ አንተ መጥፎ ፈላጊ ሆይ! (መጥፎ ስራህ) ተቆጠብ” የሚል ተጣሪ ይጣራል። አላህ ከእሳት ነጻ የሚያደርጋቸው አሉ። ይህ በሁሉም (የረመዷን) ሌሊቶች ነው።” *(ቲርሚዚይ፡ 682, ብን ማጀህ፡ 1642)*

“አንተ መልካም ፈላጊ ሆይ! (ፊትህን አላህን ወደመታዘዝ) አዙር” የሚለውን የረሡል ﷺ ንግግር አስተውል! አንተ አላህን ለመታዘዝ ምቹ የሆነውን መልካም ወር ተቀብለሃልና ሙሉ በሙሉ ለዒባዳ ፊትህን አዙር ማለት ነው። ለዒባዳ ታላቅ ፍላጎትና ጉጉት ይኑርህ። ነፍስ ከዚህ ትርፋማ ወር እንዳትከስር አደራ ተጠንቀቅ! ይህ አትራፊ የሆነ መልካም ወር ነው። እርሱ ካመለጠ መመለስ አይቻልም።

“አንተ መጥፎ ፈላጊ ሆይ! (ከመጥፎ ስራህ) ተቆጠብ” ከዚህ በፊት ስትሰራው የነበረውን

መጥፎ ተግባር አሁንም በዚህ የተከበረ የረመዷን ወር ለማስቀጠል የፈለገች ነፍስ ሁኔታው ተስማሚ ባለመሆኑ በጥመቷ ላይ ወሰን ልታልፍ አይገባም ማለት ነው።

በዚህ የተከበረ የበረካ ወር ፊቱን ወደአላህ በማዞር ያልተጸጸተ ነፍሱ ለዚህ ነገር ያልተንቀሳቀሰች መቼ ልትንቀሳቀስ ነው? በርካታው ሰው ለዱንያም ይሁን ለአኼራው በማይጠቅሙና ከመልካም ስራ በሚያዘናጉ ጉዳዮች ተጠምዷል። ይህ ደግሞ ጸጸት አድርጎ ወደአላህ እንዳይመለስ እንቅፋት ይሆንበታል። በምቾት ላይ ሆኖ ያነጋል ያመሻል። ጊዜውን በማይረባ ነገር ያባክናል። ይጫወታል ፣ ቀልድ ይቀልዳል ፣ ወሬ በማውራት በእንቅልፍ በስንፍና ሰዎችን በማማት ድንበር በማለፍ ሌሊቱን ያነጋል።

ይህ የተከበረ የበረካ ወር ለእነዚህ አይነቶቹ ዝንጉ ሰዎች ትክክለኛ ተውበት ለማድረግ ፣ ፊታቸውን ወደአላህ ዒባዳ ለመመለስ ትልቅ ድርሻ አለው። በዚህ የተከበረና ትልቅ በሆነ ወር ውስጥ ነፍሱ ለጸጸት ካልተንቀሳቀሰች መቼ ልትንቀሳቀስ ነው? ባሪያው በዚህ ወር ፊቱን ካላዞረ መቼ ሊያዞር ነው?

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

“አላህ ከእሳት ነጻ የሚያደርጋቸው አሉ። ይህ በሁሉም (የረመዷን) ሌሊት ነው።” አላህ በዚህ የተከበረ ወር በሁሉም ሌሊት ከጀሐነም ነጻ የሚያደርጋቸው ሰዎች አሉ። የሙስሊም ነፍስ ይህን ታላቅ የሆነ የአላህ ቃል ኪዳን ለመጎናጸፍ መቋመጥ ይኖርባታል።

በአንዳንድ ቦታዎች ውድድር ሲካሄድ አስተውላችኋል? ለውድድሩ የሽልማት ማስታወቂያ ይሰራል። ይህን ውድድር በቀዳሚነት ላለፉ ሰዎች ለእያንዳንዱ ቀን አንድ አንድ ሽ ሪያል ወይም ከዚያ በላይ ወይም ከዚያ ያነሰ ሽልማት ይሰጣል ይባላል።

ሰዎች ሽልማቱን ለማግኘት በጣም ይቋምጣሉ ፤ በጣም ይሽቀዳደማሉ። ሁሉም ከአሸናፊዎች ለመሆንና አንድ ሽ ሪያል ወይም ከዚያ ያነሰ ወይም ከዚያ የበዛ ገንዘብ ለማግኘት ነፍሱን ለዚያ ውድድር መስዋዕት ያደርጋል። የአኼራ ውድድር ሲሆን ግን ምንዳው በትንሳዔ ቀን ስለሆነ ለዚህ የተከበረ ጉዳይ ፍላጎቱ ይቀንሳል ፣ ምኞቱ ይደክማል። ካለበለዚያማ አንድ ሙስሊም "አላህ ከእሳት ነጻ የሚያደርጋቸው ባሮች አሉ" የሚለውን የረሡል ﷺ ንግግር ሲሰማ ተሽቀዳድሞ ከእነዚያ ሰዎች ለመሆን ከፍተኛ ፍላጎት ሊኖረው ይገባ ነበር። የውድድሩ ቀዳሚ ለመሆን ከፍተኛ ጥረትና ትግል ማድረግ ነበረበት። አላህን ከእሳት ነጻ እንዲያደርገው ፣ በዚህ የተከበረ የአላህ ቃል - ኪዳን ከሚጎናጸፉት ለመሆን ወደአላህ ፊቱን ማዞር ነበረበት።

ረሡል ﷺ ይህንን የተከበረ የረመዷን ወር የትዕግስት ወር ብለው ሰይመውታል።

"የትግስት ወርን ጾሞ ከየወሩ ደግሞ ሶስት ቀናቶችን የጾመ አንድ አመት እንደጾመ (ይቆጠርለታል።) " *(አህመድ፡ 7567, ነሳኢ፡ 2408)*

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የትዕግስት ወር ብለው መግለጻቸው ይህ የተከበረ ወር ለሙስሊም መልካም ነገሮችን የሚጎናጸፍበት ብሎም በዚህ ወር ውስጥ ነፍሱ በርካታ የትዕግስት አይነቶችን የምትለማመድበት ወር መሆኑን ለመግለጽ ነው። አላህ ያዘዛቸውን ነገሮች ለመፈጸም ትዕግስት ያስፈልጋል ፤ ከልከል ያደረጋቸውን ነገሮች ለመታቀብ ትዕግስት ያስፈልጋል ፤ አላህ በወሰናቸው የትኛውም አይነት ውሳኔዎች ላይ መታገስ ያስፈልጋል።

ይህ ወር የትዕግስት ወር ነው። አላህ ታጋሾችን ያለሂሳብ ወይም ተቆጥሮ በማያልቅ ምንዳ ይመነዳል። ሙስሊም ይህ ወር ከገባበት ቀን አንስቶ ወሩ እስኪያልቅ ድረስ

ትዕግስት በሚጠይቁ ዒባዳዎች - በአምልኮ ፣ በመታዘዝ ፣ በዚክር ፣ በቁርኣን ፣ በሶላት ፣ በጾም እና በመሳሰሉት ትዕዛዛቶች - ነፍሱን ያለማምዳታል።

በዚህ የተከበረ ወር ነፍሱን የአላህን ትዕዛዝ ከመንቀፍ ፣ የለመደውን ነገር - ምግብ ፣ መጠጥ እና የመሳሰሉ ነገሮችን - በመተው ነፍሱን ያስታግሳት።

አንድ ሙስሊም በዚህ የተባረከና የተከበረ የረመዷን ወር አላህን ፈርቶ ከእርሱ የሚያገኘውን ምንዳ ታሳቢ አድርጎ የተፈቀዱ ነገሮችን መከልከል ከቻለ ፤ ሀራም ነገሮችን የተዳፈሩ ሰዎች የሚያጋጥማቸውን ቅጣት ታሳቢ በማድረግ ክልክል ነገሮችን በዘውታሪነት ሊከለከል ይገባዋል።

ነፍሱ አሳማሚ ከሆኑ የአላህ ውሳኔዎች እንድትታገስ ያለማምዳት። ነፍስ እየቋመጠች ምግብን ፣ መጠጥን መተው እንደዚሁ አላህ ከፈቀደው ፣ ስሜት ከምትፈልገው ጣፋጭ ነገሮች ሁሉ መቆጠቡ ትዕግስትን ለማረጋገጥ አጋዥ ይሆናል።

አንድ ሙስሊም ተጀምሮ እስከሚያልቅ በዚህ የተከበረ ወር ታላቅ የትዕግስት ትምህርትን ፣ የመልካም ስራ አይነቶችን ተለማምዶ ይወጣል። ጥቅሙ ወይም በረከቱ በዚህ ወር ብቻ የተገደበ አይደለም። ነፍሱን ትዕግስት ካለማመዳት ፤ የትዕግስትን ህይዎት ከኖረ የዚህ ወር በረከት በአጠቃላይ ለእድሜ ልኩም ያገለግለዋል። በዚህ ታላቅ ወር ትዕግስትን በመለማመድ ካልተሸለመ መቼ ትዕግስትን ሊለማመድ ነው?

በመሆኑም በዚህ የተከበረ ወር አላህ ያዘዘውን ነገር በመተግበር መታገስ ፣ እርሱ የከለከላቸውን ነገሮች በመከልከል ላይ መታገስ እና አላህ ከወሰናቸው አሳማሚ የአላህ ቅጣቶች መታገስ እያንዳንዱ ሙስሊም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

ረሡል ﷺ ይህን የተከበረ ወር የበረካ ወር ብለው ገልጸውታል፡፡

“የተባረከው ወራችሁ መጣላችሁ፡፡ አላህ በእናንተ ላይ መጾምን ግዴታ አድርጓል፡፡ የጀነት በሮች ይከፋፈታሉ ፤ የእሳት በሮች ይዘጋጋሉ፡፡ የሰይጣን አመጸኞች ይታሰራሉ፡፡” (ነሳኢይ ፡ 2106)

በዚህ ሐዲስ የተፈለገው መልዕክት ረሡል ﷺ ይህን ወር የተባረከ በሚል መግለጻቸው ነው፡፡ የዚህ ወር በረካ ከተጀመረ ጀምሮ እስኪያልቅ በየሰዓቱ ፣ በየደቂቃው እና በየሰከንዱ የሚገኝ በመሆኑ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቅጽበት በታላላቅ መልካም ተግባራት ፣ ትሩፋትና በረከቶች የተሞላ ነው፡፡

ከዚህ ወር በረከቶች መካከል ነብዩ ﷺ በዚህ ሐዲስ ላይ - የጀነት በሮች ይከፋፈታሉ ፤ የእሳት በሮች ይዘጋጋሉ ፤ አመጸኞቹ ሰይጣናት ይታሰራሉ በማለት የተናገሩት ነው፡፡ ይህ በሌሎች ወሮች የማይገኝ በዚህ ወር ብቻ የምናገኘው ልዩ የሆነ በረከት ነው፡፡ የጀነት በሮች አይዘጉም ፣ ሁሉም ይከፈታሉ፡፡ የእሳት በሮች አይከፈቱም ፣ ሁሉም ይዘጋሉ፡፡ አመጸኛ ሰይጣናት ይታሰራሉ፡፡ ሰይጣናት በሌሎች ወሮች ሰዎችን ወደመጥፎ ጎዳና እንደሚጎተጉቱት በዚህ ወር መጎትጎት አይችሉም፡፡

ለመልካም ስራ ቆራጥ መሆን ፣ ያለን ፍላጎት መጨመር ፣ በአላህ ትዕዛዝ ላይ ቀጥ ለማለት ፊትን ማዞር የዚህ ወር ታላቅ በረከት ነው፡፡

የዚህን ወር መልካም ተግባራት ፣ ደረጃ ፣ ትሩፋት እንዘርዝር ብንል ቦታው አይበቃንም፡፡ ነገር ግን ይህን ወር እንዴት መቀበል አለብን በሚለው ዙሪያ ለአንባቢያን የተወሰኑ አንገብጋቢ ነጥቦችን ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡

1. በቅድሚያ ይህ የተከበረ ወር ሲገባ እኛ ሙስሊሞች ከፍተኛ የሆነ ደስታ ሊሰማን ይገባል። ለዚህ ወር በልባችን ትልቅ ቦታ፣ ትልቅ ደረጃ ልንሰጠው ይገባል። አላህ ለዚህ ወር በሰላም ስላደረሰን አለህን ልናመሰግን ይገባል። ይህ የአላህ ስጦታና በረከት ነው። ያለፈው አመት ረመዷን የነበሩ ነገር ግን መጭውን ረመዷን ለማግኘት እየቋመጡ በሞት ምክንያት የተለዩን ስንት ወንድሞችና እህቶች ናቸው? አሁንም ቢሆን እኛ አናውቅም ከመካከላችን የተወሰነው ሰው ይህን መጭውን ረመዷን ላያገኘው ይችላል ፤ ከፊላችን ደግሞ ልናገኘው እንችላለን።

ያለምንም ጥርጥር በጤና ፣ በሰላም ፣ በኢማን የረመዷንን ወር መድረስህ ለአንተ ታላቅ የሆነ ጸጋ ፤ ታላቅ የሆነ የአላህ ውለታ ነው። የተከበረውን ወር ክብር ፣ ምንነትና ደረጃ ልታውቅ ይገባሃል። ይህን ታላቅ ወር ስላደረሰህ አላህን ለመታዘዝ መነሳሳትህ ፣ የአላህን ሐቅ ለማድረስ ከውስጥህ ፍላጎት መኖሩ የአላህን ጸጋ ከማመስገን ነው። ስለዚህ በዚህ ወር ውስጥ ጾም አለ ፣ ሌሊት ቆሞ መስገድ አለ ፣ በመልካም ስራዎች ወደአላህ መቃረብ አለ ፣ ከህራም ነገሮች መራቅ አለ በእነዚህ ተግባራት ሁሉ የዚህን ወር ክብር በመረዳት አላህን በመገዛት ላይ ቀጥ ልትል ይገባሃል።

ነብዩ ﷺ አዲስ ጨረቃ ሲመለከቱ የሚከተለውን ይሉ ነበር፡-

"አላህ ሆይ ይህን ጨረቃ በእኛ ላይ በበረከት ፣ በኢማን ፣ በሰላም እና በኢስላም አውጣው ፣ (ጨረቃውን) የእኔ ጌታ የአንተም ጌታ ነው (ይሉት ነበር)።"

(ቲርሚዚይ፡ 3451, አህመድ፡ 1397)

ጨረቃውን በመመልከት ይህ የተባረከ ወር በአንተ ላይ መግባቱን ካረጋገጥክና አላህ በእርሱ ካላቀህ ከላይ ነብዩ ﷺ ያደረጉትን ዱዓ አድርግ።

ይህ ዱዓ ትልቅ ዱዓ ነው። ወርህን አላህ ለአንተ የበረከት ፣ የሰላም ፣ የኢማን ወር እንዲያደርግልህ ፤ የእርሱን ሐቅ ቀጥ አድርገህ ለመፈጸምና ከመጥፎ ነገሮች እንዲጠብቅህ ጌታህን ጠይቅ። ለዚህ ወር በሰላም ስለደረስክ አላህን ማመስገንህ ግዴታ የሆነባት ታላቅ ጸጋ መሆኑ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። ስለዚህ ይህን ወር ተገቢ የሆነ ክብር ልትሰጠው ይገባል።

2. ይህን የተከበረ ወር ከማንኛውም ወንጀል እና ሐጢያት ትክክለኛ ጸጸት በማድረግ ልንቀበለው ይገባል። ሁላችንም ሐጢያተኞች ነን ፤ ከሰው ልጅ ወሰን መተላለፍ ፤ ጥፋት ፣ ጉድለት መከሰቱ የማይቀር ነው።

ከነብዩ ﷺ የሚከተለው ሐዲስ መጧል።

“ማንኛውም የሰው ልጅ ተሳሳች ነው፤ ከተሳሳቾች መልካሙ ጸጸት አድርጎ የሚመለሰው ነው” *(ቲርሚዚይ፡ 2499, ኢብኑ ማጀህ፡ 4251)*

የረመዷን ወር ተውበት የምናደርግበት ታላቅ ወር ነው። ስንት ሰዎች አሉ የአላህን ህግ በመጣስ ወሰን የተላለፉ ፣ በርካታ ክልክል ነገሮችን የፈጸሙ። ነገር ግን ይህ ወር ከገባ ጀምሮ ነፍሳቸው አላህን ለመታዘዝ ፣ ለመልካም ስራዎች ትነሳሳለች። በዚህ ምክንያት ጉድለታቸውን አምነው በልቦቻቸው ውስጥ ጸጸትን በማስገኘት ፊታቸውን ወደአላህ ያዞሩ ሰዎችን ቁጥር ቤቱ ይቁጠረው።

ስንት ሰዎች ናቸው በዚህ የተከበረ ወር ትክክለኛ ተውበት አድርገው ከዚያ በኋላ ወደነበሩበት ወንጀል ያልተመለሱ?

ጉድለት ያለበት ፣ ያጠፋ ያከፋ ነፍሱን በዚህ የተከበረ ወር እንድትጸጸት ካላደረገ መቼ ጸጸት ሊያደርግ ነው? ይህ ወር ነፍሱን ካላንቀሳቀሰለት የትኛው ወር ነው

ሊያንቀሳቅስለት የሚችለው?

የረመዷን ወር ወደአላህ ጸጸት አድርገን የምንመለስበት ታላቅ ወር ነው። ስለዚህ ከማንኛውም ወንጀል በትክክለኛ ጸጸት እንቀበለው።

ትክክለኛ ጸጸት ካልሆነ በቀር አላህ ከባሮች ጸጸትን አይቀበልም። ትክክለኛ ጸጸት የሚባለው የግድ ሶስት መስፈርቶችን ያሟላ መሆን አለበት።

- ወንጀል በመስራቱ መጸጸት
- ወደወንጀል ላለመመለስ ቁርጠኛ መሆን
- ሙሉ በሙሉ ከወንጀል መላቀቅ ናቸው።

አንድ ሰው በእነዚህ ሶስት መስፈርቶች መሰረት ጸጸት ካደረገ አላህ ጸጸቱን ይቀበለዋል።

የእውቀት ባለቤቶች ወንጀሉ ከሰው ልጆች ጋር ተያያዥነት ካለው ከእነዚህ ሶስት መስፈርቶች በተጨማሪ አራተኛ መስፈርት እንዳለ ይናገራሉ። ለምሳሌ ገንዘብ የወሰደ ሰው ጸጸት ማድረግ ከፈለገ ከላይ ከዘረዘርናቸው ሶስት መስፈርቶች በተጨማሪ የግድ ገንዘቡን ለባለቤቱ መመለስ አለበት።

ከማንኛውም ወንጀልና ሓጢያት በትክክል ጸጸት አድርገን የምንመለስ አላህ ያድርገን!!

3. በዚህ የተከበረ ወር ሌላው ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ ግዴታ ያደረገብንን ጾም ልንጠብቅ ነው። በእርግጥ ሰዎች ከፈጅር ጀምሮ ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ከምግብ ፣ ከመጠጥ ፣ ከሌሎች አስፈጣሪ ነገሮች በመቆጠብ ተመሳሳይ ቢሆኑም

ጾማቸውን በማሟላት በመካከላቸው ታላቅ ልዩነት አላቸው።

“በምንዳ የትኛው ጾመኛ ነው ከፍተኛው” የሚል ጥያቄ ረሡል ﷺ ተጠየቁ።

“አላህን በብዛት የሚዘክር ነው” የሚል ምላሽ ሰጡ። *(አህመድ፡ 15614)*

በእርግጥ ጾመኞች ወደአላህ ዚክር ፣ ቁርኣን በመቅራት ፣ የአላህን ትዕዛዝ ተጠባብቆ በመተግበር ፊታቸውን በማዞር ከፍተኛ የሆነ መበላለጥ አላቸው።

ከሰዎች መካከል የሌሊት ወቅታቸውን በማይረባ ነገር በማሳለፍ ሱብሂን ሶላት የሚያሳልፉ ወይም ሰጋጆች ከሆኑም በእንቅልፍ ላይ ሆነው የሚሰግዱ ሰዎች አሉ። አንዳንዶች የዙሁርን እና የዓስርን ሶላት ከወቅቷ የሚያስመልጡም አሉ።

በጾም ባህሪ ላይ ሰዎች ታላቅ መበላለጥ አላቸው። ስለዚህ እያንዳንዱ ሙስሊም ጾሙን በማሟላት ሊጾም ፣ አላህን በአግባቡ ሊዘክር ፣ ወደአላህ ዒባዳ ፊቱን በማዞር ላይ ከፍተኛ ስሜት ሊኖረው ይገባል። ይህን ወር ቁርኣን በመቅራት ፣ መልካም ስራዎች በሚሰሩበት ቦታ ቀድሞ መገኘት ፣ መስጅድን በማዘውተር ነፍሱን ሊያስታግሳት ይገባል።

4. ሌላው አንገብጋቢ ጉዳይ በዚህ የተከበረ የጾም ወር የሚከተለውን የረሡል ﷺ ንግግር ተግባራዊ ማድረግ ነው።

“አምኖ ከአላህ ዘንድ የሚገኘውን ምንዳ ታሳቢ አድርጎ የረመዷንን ጾም የጾመ ከዚህ በፊት ያከፈውን ወንጀል ይማራል።” *(ቡኻሪ፡ 1875, ሙስሊም፡ 1268)*

አንድ ሙስሊም ሰዎች በልምድ ስለፈጸሙት ሳይሆን አምኖ እና ከአላህ ዘንድ የሚገኘውን አጅር ታሳቢ አድርጎ የረመዷንን ወር ሊጾም ይገባል።

ቤተሰቦቹ ወንድሞቹ ጓደኞቹ ስለጾሙት ወይም "እከሌ በረመዷኑ ይበላል እንዴ?" እንዳይባል ወይም ለሰዎች እይታ ወይም ለእነርሱ ውዳሴ ብሎም መጾም የለበትም። መጾም ያለበት አምኖ ከአላህ ዘንድ የሚገኘውን አጅር ወይም ለጾመኞች "አላህ አጅራቸውን ያለግምት በተሟላ ሁኔታ ይሰጣቸዋል" የሚለውን የአላህ ቃል-ኪዳን አምኖበትና ፈልጎ እንዲሁም አላህ ለባሮች ግዴታ ያደረገው መሆኑን አምኖ መጾም አለበት።

"ኢህቲሳብ" ወይም በዚህ ወር የሚገኘውን ታላቅ ምንዳ ታሳቢ አድርጎ ወይም ጾሙን የአላህን ትዕዛዝ ለመፈጸም ብሎ ይጹም።

ጾመኞች ታላቅ ምንዳ እንዳላቸው አላህ በሀዲሰል ቁድስ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

"ጾም የኔ ነች እኔው ነው የምመነዳው" *(ቡኻሪ፡ 1761)*

ይህ ሐዲሰል ቁድስ የጾመኞች ምንዳ ታላቅ መሆኑን ግልጽ ያደርጋል። ስለዚህ ሙስሊሞች ጾማቸውን አጥብቀው ሊጾሙ ይገባል።

በሌላ ሐዲስ ደግሞ የአላህ መልክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"ለጾመኞች ሁለት ደስታዎች አሏቸው። ሲያፈጥር ይደሰታል ፤ ጌታውን ሲገናኝ ይደሰታል።" *(ቡኻሪ፡ 1771)*

ጾመኛ ለወደፊት ጌታውን በሚገናኝ ጊዜ ታላቅ የሆነ ደስታ ይደሰታል። ምክንያቱም አላህ ለጾመኞች ታላቅ ምንዳ አዘጋጅቷል። ይህ ብቻ አይደለም ከነብያችን ﷺ በትክክለኛ ሐዲስ እንደተረጋገጠው ጾመኞችን **"ረያን"** በተባለ ልዩ የጀነት በር ያስገባቸዋል። *(ቡኻሪ፡ 1896)*

ስለዚህ ሙስሊሞች ይህን የተከበረ የረመዷን ወር ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ከአላህ ዘንድ የሚገኘውን አጅር ታሳቢ አድርገው በእነርሱ ላይ አላህ ግዴታ ያደረገባቸው መሆኑን አምነው ሊጾሙ ይገባል።

5. ሌላው አንገብጋቢ ጉዳዩ በዚህ የተከበረ የረመዷን ወር ጾም የተደነገገበት ዋና ዓላማ የሆነውን የአላህ ፍራቻ ማስገኘት ይገባናል።

አላህ በተከበረው ቁርዓን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ﴾

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ ልትጠነቀቁ ዘንድ" *(አል'በቀራህ፡ 183)*

በዚህ የረመዷን ወር ዒባዳን በመፈጸም የአላህን ፍራቻ የሚያገኙበትን ጎዳና ይጓዛል። የረመዷን ወር አላህን ከሚፈሩት ተርታ ለመሰለፍ ፣ የእርሱን ፍራቻ ለመጎናጸፍ የሚያግዝ ትልቅ ወር ነው።

"ተቅዋ" (አላህን መፍራት) ፡ ማለት *"በአላህ ትእዛዝ ከአላህ በሆነ ብርሃን ከአላህ ያለውን ምንዳ ተስፋ አድርጎ መስራት ፣ በአላህ ብርሃን የአላህን ቅጣት ፈርቶ ወንጀልን መተው ማለት ነው።"*

እስኪ ጾም ለባሪያው ተቅዋን እንዴት እንደሚያረጋግጥለት? በውስጡ በተቅዋ ስንቅ እንዴት እንደሚሰነቅ? የተወሰነ ቆም ብለን እናስተውል! ሙስሊም በአመቱ ውስጥ በየቀኑ ብዙ ነገሮችን መጠቀምን ለምዷል። በጧት ቁርስ ፣ ቀን ላይ ደግሞ ምሳ ይበላል ፣ የሚጠጡ ነገሮችንም ይወስዳል።

እነዚህን የተለመዱ ነገሮች በተሟላ ሁኔታ የረመዷን ወር ከገባ ጀምሮ ይተዋቸዋል። ከአላህ ዘንድ የሚገኘውን ምንዳ ታሳቢ አድርጎ የለመዳቸውን የተፈቀዱ ነገሮች ሙሉ በሙሉ ይተዋቸዋል ፤ ከእነርሱም ይከለከላል። ይህ ነው ተቅዋ ማለት ። አንድ ጾመኛ ሙስሊም ሰው ከማያየው ቦታ ሆኖ ከምግብ ፣ ከመጠጥ ተቆጥቦ ታየዋለህ። ለምን ብሎ ነው? ከአላህ የሚገኘውን ምንዳ ፈልጎ ፤ አላህን ለመታዘዝ ብሎ ነው።

አንድ ሙስሊም ይህን በረመዷን ወር ያገኘውን መልካም ባህሪ - አላህ ያዘዘውን ለመፈጸም የከለከለውን ለመከልከል ያሳየው ዝግጁነት - የሁልጊዜ ባህሪው ሊያደርገው ይገባል።

አንተ አላህን ለመታዘዝ ብለህ በረመዷን ወር ከምግብ ከመጠጥ ተከልክለሃል። አዎ! በሌላም ጊዜ አላህ ከከለከለው ሁሉ መከልከል የአንተ ባህሪ ሊሆን ይገባል። የረመዷን ጌታ የሁሉም ወሮች ጌታ ነው። በረመዷን ከታዘዝነው በማንኛውም ወቅት ልንታዘዘው ይገባል። አንተ በረመዷን ወር አላህን ለመታዘዝ ብለህ ነፍስህን ተቆጣጥረሀት ፣ ከወንጀል አግተሃት ፣ የለመድከውን በእርግጥ ትተህ ከሆነ አሁንም በማንኛውም ወቅት የለመድከው ነገር ካለ መተውን ለነፍስህ ልታስለምዳት ይገባል።

ከፈጅር አንስቶ ፀሀይ እስክትወጣ ከምግብ ፣ ከመጠጥ ፤ እንዲሁም ከማንኛውም አስፈጣሪ ነገሮች የመከልከሉ ግዴታነት በረመዷን ወር ብቻ ነው። ከሀራም ነገሮች ወይም ክልክል ነገሮች መጾም ወይም መቆጠብ ግን የእድሜ ልክ ስራ ነው።

በተሟላ ሁኔታ አላህ ክልክል ካደረገው ሁሉ በመጾም ወይም በመቆጠብ ነፍስህን ልትታገል ይገባል። ከአንተ ዘንድ የሆነ ጉድለት ከተከሰተ ወደአላህ ተውበት በማድረግ ነፍስህን ተቆጣጠር።

ከዚህ ላይ አላህን በመፍራት ከረመዷን ወር እንዴት ተጠቃሚ እንሆናለን? የሚለውን ነቃ ብለን መከታተል አለብን። አንድ ሰው ለአላህ ብሎ ከተለመዱ ነገሮች ሲከለከል እናስተውላለን። በማንኛውም ወቅት ከሀራም ነገሮች ለምን አይከለከልም? ከቀደምቶች አንዱ አላህን ስለሚገዙ ማህበረሰቦች ጥያቄ ቀረበለት። በረመዷን ፈርድም ይሁን ዋጅብ ነገሮችን ይጠብቃሉ ነገር ግን ረመዷን ሲወጣ ከዚህ ሁሉ ይርቃሉ?

"በረመዷን እንጅ አላህን የማያውቁ ሰዎች ከፉ" በማለት ምላሽ ሰጠ። *(ለጧኢፉል መዓሪፍ፡ ገጽ 396)*

አንድ ሙስሊም በረመዷንም ይሁን በሌላ ጊዜ አላህ ግዴታ ያደረገበትን ነገር ተጠባብቆ የመስራት ግዴታ አለበት። አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ﴾

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጻም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ህዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ ልትጠነቀቁ ዘንድ" *(አል'በቀራህ፡ 183)*

ይህ ማለት በረመዷን ውስጥ የአላህን ትዕዛዝ በመፈጸማችሁ የእርሱን ፍራቻ ልታገኙ ዘንድ ማለት ነው። በዚህ ምክንያት የረመዷን ወር የአላህ ፍራቻ ለመሰነቅ ትልቅ ወር ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَتَزَوَّدُواْ فَإِنَّ خَيْرَ الزَّادِ التَّقْوَى وَاتَّقُونِ يَا أُوْلِي الأَلْبَابِ﴾

“ተሰነቁም ፤ ከስንቅም ሁሉ በላጩ ጥንቃቄ (አላህን መፍራት) ነው። የአዕምሮዎችም ባለቤቶች ሆይ ! ፍሩኝ” *(አል’በቀራህ ፡ 197)*

﴿إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ﴾

“አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው።” *(አል’ሁጁራት፡ 13)*

ውድ የሆነው እድላችን በዚህ የተከበረ ወር ለአላህ ፍራቻን መሰነቅ ነው። ከረመዷን መድረሳ አላህን ፈሪዎች ፣ የአላህን ትዕዛዝ በመፈጸምና በመጠባበቅ ተለማማጅዎች ሆነን ተመርቀን ልንወጣ ይገባል።

በርካታ ሰዎች በጣም አስደናቂ ባህሪ ይስተዋልባቸዋል። ረመዷን ሲገባ መስጅዶችን ይሞላሉ ፣ ሶላትን ተጠባብቀው ይሰግዳሉ። ረመዷን ሲወጣ ሙሉ በሙሉም ይሁን በከፊል መስጅዱን ይሰናበታሉ። በረመዷን የፈጅር ሶላት ሁለት ወይም ሶስት ሶፍ ሲሞላ የነበረው አንድ ሶፍ ሳይሞላ ይቀራል። በረመዷን ወር ተገኝተው ፣ ከረመዷን ውጭ የሚጠፉት ሰዎቹ የት ሄዱ? ሰዎቹ ሞቱ እንዴ? ወይስ ተሳፍረው ወደሌላ ቦታ ሄዱ? በረመዷን ወር እንጅ በሌሎች ወራቶች ዒባዳቸውን ጠብቀው የማይፈጽሙት ለምንድን ነው?

በዚህ የተከበረ የረመዷን ወር አላህ ያከበረው ፣ ሶላትን ጠብቆ ለመስገድ እድለኛ የሆነ ፣ ነፍሱ የአላህን ትዕዛዝ ለመፈጸም የተንቀሳቀሰች ፣ የዒባዳን ጣፋጭነት የቀመሰ ማንኛውም ሙስሊም ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ በሌላው ቀሪ

የህይዎት ዘመኑ ሁሉ በዚሁ ባህሪ ላይ ሊቀጥል ይገባል።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ﴾

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ህዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ ልትጠነቀቁ ዘንድ" *(አል'በቀራህ፡ 183)*

ይህ ማለት በዚህ የተከበረ ወር ውስጥ በምትፈጽሙት የአላህ ዒባዳና ትዕዛዝ አላህን ልትፈሩ ዘንድ ማለት ነው።

በዚህ መሰረት፡ ጾም በዲን ተኮትኩተው የሚያድጉበት ፣ በህይዎታቸው ሁሌም ይዘውት የሚጓዙት ስንቅ ተሰንቀው አላህን የሚፈሩ አማኞች የሚወጡበት የተባረከ ትልቁ መድረሳ ነው። ይህ መድረሳ የጾም ወር መድረሳ ነው። ነገር ግን በርካታው ሰው ከእርሱ ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም። ይህ የተላቀ እና የተከበረ ወር ሳይጠቀሙበት በእነርሱ ላይ በከንቱ ያልፋል። እነርሱ ልክ በአንድ መድረሳ አንድ ደደብ ተማሪ ውጤታማ ሳይሆን እንደሚባረረው ማለት ናቸው።

ጠንካራ ፣ ቁምነገረኛ የሆነው ሙእሚን በዚህ የተባረከ መድረሳ ገብቶ ለቀጣይ ህይዎቱ ሁሉ በሚያገለግል ኢማናዊ የዲን እውቀት ታንጾና ተኮትኩቶ ይወጣል።

ከረመዷን ትምህርቶች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል።

እርኩስ እና ቆሻሻ የሆነ ፣ ምንም አይነት ጥቅም የማያስገኝ የሆነውን ሲጋራ በማጨስ የተፈተነ ሰው በዚህ የተከበረ ወር ከፈጅር እስከ ፀሀይ እስክትወጣ ሲጋራን በተሟላ ሁኔታ ተከልክሎ ይውላል። አስካሪ መጠጥ የሚጠጣው ሰው

በተመሳሳይ ተከልክሎ ይውላል። በእውነት ካስተዋልነው እንዲህ አይነት ሱስ ያላቸው ሙስሊሞች ሙሉ በሙሉ ለመተው ይህ የተከበረ ወር ትልቅ እድል ሰጧቸዋል። በርካታ ሲጋራ አጫሾች “ለምን ታጨሳለህ?” ሲባል የሚሰጠው ምክንያት “መተው አልችልም” የሚል ነው። በዚህ የተከበረ ወር ከፈጅር ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ተከልክለህ አልዋልክምን? የሚል ጥያቄ እንጠይቀዋለን። ይህ ፣ በእርሱ አቅም እና ችሎታ ከዚህ የሲጋራ ሱስ ሙሉ በሙሉ መከልከል እንደሚችል ማሳያ ነው።

በጣም የሚያስገርመው ደግሞ አንዳንድ ሰዎች ጾመው ውለው በሲጋራ የሚያፈጥሩ አሉ። ከተፈቀዱ ነገሮች ጾሞ አላህን ሲታዘዝ ውሎ ሙዓዚኑ ለመግሪብ ሶላት አዛን ባደረገ ጊዜ በሀራም ያፈጥራል። አንዳንዶቹ ደግሞ ማፍጠሪያ ሰዓት ሲጋራ አጭሰው መግሪብ ላይ በመጥፎ ሽታ ሰጋጆችን መላኢካዎችን የሚያስቸግሩ አሉ። ጥመታቸው ወሰን ያለፈ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ሲጋራውን ከመስጅድ በር የሚያጠፉ አሉ።

በዚህ አይነቱ ግለሰብ ተደነቅ። ቀን ሙሉ አይበላም ፣ አይጠጣም አላህን ለመታዘዝ ጾሞ ውሏል። አዛን አድራጊው አዛን እንዳደረገ በሀራም ነገር ለማፍጠር ይሽቀዳደማል። ሲጋራ ማጨስ ወንጀል ነው ፣ ሀራም ነው። አላህ በዚህ ላይ ሂሳብ ያደርገዋል። በዚህ ወንጀሉ ይቀጣል። ሀራም ለመሆኑ ዑለሞች በርካታ መረጃዎችን በማቅረብ በስፋት ሂደውበታል።

ረመዷን የሚያጨሱ ሰዎች ተጸጽተው ለመመለስ ትልቅ እድል ነው። ማንኛውም ወሰን አላፊ ፣ ያጓደለ ፣ ያጠፋ ሁሉ ይህ የተከበረ ወር ተጸጽቶ ለመመለስ ትልቅ

በመሆኑ ሊጠቀምበት ይገባል።

6. በዚህ ወር ተፈጻሚ ከሚሆኑ አንገብጋቢ ጉዳዮች መካከል ለአላህ ኪታብ ትኩረት መስጠት ነው። ከረመዷን ልዩ ገጽታው መካከል ቁረኣን በዚህ የተከበረ ወር መውረዱ ነው። አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿شَهْرُ رَمَضَانَ الَّذِي أُنزِلَ فِيهِ الْقُرْآنُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَاتٍ مِّنَ الْهُدَى وَالْفُرْقَانِ﴾

"(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲሆን ቁርኣን የተወረደበት የረመዷን ወር ነው።" *(አል'በቀራህ፡ 185)*

በዚህ ወር ቁርኣን ወረደ። ጅብሪል ወደነብዩ ﷺ በመምጣት ቁርኣንን ያስተምራቸው ነበር። ነብዩ ﷺ በእርሱ ላይ ቁርኣንን ያነባሉ ፣ እርሱም ያደምጣቸዋል። *(ቡኻሪ፡ 6, ሙስሊም፡ 2308)*

እያንዳንዱ ሙስሊም በዚህ ታላቅ የቁርኣን ወር በአላህ ኪታብ ላይ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። ኣንዳንድ ሰለፎች የረመዷን ወር በገባ ጊዜ ስራቸውን ሙሉ በሙሉ ይተዋሉ። በዚህ ወር "ቁርኣን መቅራት ምግብ ማብላት ነው።" በሚል መርሆ ወደቁርኣን ይዞሩ ነበር። ከእነርሱ መካከል በየቀኑ ፣ በየሶስት ቀኑ ፣ በየሳምንቱ ፣ በየአስር ቀን ቁርኣንን የሚያጠናቅቁ ነበሩ።

ከሰዎች መካከል ረመዳን ገብቶ እስኪወጣ የተጠመዱት በሌላ ጉዳይ በመሆኑ ቁርኣንን አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ወይም ሶስት ጊዜ እንኳ ከፍተው የማያውቁ አሉ።

እኔንም እናንተንም በዚህች ጽሑፍ ተጠቃሚ እንዲያደርገን ፤ ከመልካም ሚዛናችን ላይ እንዲጽፍልን ፣ በእኛ ላይ ማስረጃ ሳይሆን ለእኛ ማስረጃ እንዲያደርጋት ፤ እኛንም እናንተንም ይህን ታላቅ ወር ሱናውን በገጠመ ሁኔታ በጾም ፣ በስግደት ቁርኣን በመቅራት የምናሳልፍ እንዲያደርገን ፤ የነገራችን መጠበቂያ የሆነውን እምነታችንን ፤ በውስጧ መኖሪያችን የሆነችውን ዱንያችንን ፤ በውስጧ መመለሻችን የሆነችውን አኺራችንን እንዲያስተካከልን ፤ ህይዎታችንን የማንኛውም መልካም መጨመሪያ ፤ ሞትን ደግሞ ከማንኛውም ወንጀል ማረፊያ እንዲያደርግልን እማጸነዋለሁ።

والله تعالى أعلم

وصلى الله وسلم على نبينا محمد وعلى آله وأصحابه أجمعين

وجاء شهر رمضان

የረመዷን ወር መጣ

إعداد: الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም፡ አቡ'ዓብዱልዓዚዝ/ዩሱፍ አሕመድ

ባህር ዳር በሚገኙ የአህለሱና
መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣
ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ
መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣
ሙሐዶራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣
በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ
ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን
የቴሌግራም ሊንክ ጆይን በማድረግ
መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alateriqilhaq